የተማሪ ስም:_____ የትምህርት ዓይነት: አማርኛ
ክፍል: 6 ምደባ: _____ መንፈቅ: 1ኛ, መለማመጃ 3
ቁጥር :_____ ቀን: ታህሳስ /2016 ዓ.ም

ምንባብ

የአህያ ሆድ ከሚመስል የንጋት ቀለም ጋር ሰማይና ምድሩ ጭር ብሏል። ከአልጋው፣ከጎጆው ወጥቶ ቤቱ ግርጌ ካለችው ቁልቁል ከከበባት ጉብታ ሄዶ የሚቀመጥበትን ድንጋይ ቅዝቃዜ በእጁ ፈትሾ ቁጭ አለ። በሮቤ አቅጣጫ ሰማዩ ጠቁሯል።

አዕዋፍ ዝማሬያቸውን ጀምረዋል። ተኝተው የነበሩት ጮሬዛዎች ድምፅ በዳዲሞስ ተራራ ላይ ሲያስተጋባ ይሰማል። አልፈው፣አልፈው እንደሸምበቆ ተመዘው የወጡ ባሕርዛፎች ቅጠሎቻቸውን እንደፀናፅል ያንሻሻሉ። ከለበሰው ጋቢ ሥር ከራሱን አውጥቶ ቃኘው። አንገቱን ቀና አድርጐ በልቡ የሚያምጠው ዜማ ለመውለድ አካባቢውን በመንፈሱ ይማትር ጀመር። ከከራሩ ስልት ጋር ልቡ አብሮ መንዘር ..... መንዘር ..... እንቅልፍ ተጭኖት የነበረው ፊቱ እየተዝናና..... እየተዝናና ከአካባቢው ጋር ፍፁም ተማሰለ። ይህ ሰው ዓሊ ይባላል።

ዓሊ አምስት አመት እንኳን ሣይሞላው ነበር እናቱ የሞቱት በአብዛኞቹ የገጠር ልጆች ላይ እንደሚደርሠው ሁሉ ዓሊም እረኝነት ዕጣ ፈንታው ሆነ። አንድ ቀን ዓሊ አጭር ግራር ሥር በሐሩር ጉልበት ተሸንፎ በራበው ሆዱ ተኝቶ ሳለ ከጀሮው ራቅ፣ ወደ ጆሮው ቀረብ፣ ራቅ ቀረብ ደስ የሚል ድምፅ ሰማ ከሚያንላጅበት ቀና ሲል ድምፁ የሚመጣበትን፣ አንድ ሽማግሌ ገበሬ የሚኖሩበትን አንዲት ደሳሳ ጐጆ ፊት ለፊቱ አየ።

አንዴ ቆም ብሎ እየሠማ፣ አንዴ ወደ እሣቸው እየተጠጋ፣ ቆሞ እያዳመጠ፣ ወደ ጐጆዋ እየተጠጋ፣ እየቆመ፣ እየተራመደ፣ ፊታቸው ተገተረ። በቀኝ ክንዳቸው ስር የሸጐጧትን ጥቀርሻ የለበሰች ከራር እየገፉ ቀና ብለው በትናንሽ አይኖቻቸው አዩት። ዓሊም በፀሐይ ግለት ያብረቀረቀ የጠቆረ ፊቱን እያሸ ሽማግሌው እግር ስር ቁጭ አለ። የጳጳስ ቆብ መስሎ ከተራሮች መሀል የጐላ ተራራ ሆኖ፣ ጠፍጣፋ ምድር ላይ የተተከለው ዳዲሞስ እየመሸ ሲሄድ ግዘፈቱና ግርማው መታየቱ ቀርቶ እየሟሟ ሲጠፋ የሸማግሌው ድምፅና የከራር ግርፍ ብቻ አካባቢውን ዋጠው።

በአንድ ክንዱ ተደግፎ፣ ኦቦ ፋርጤን፣ ፊታቸውንና ሁኔታቸውን በአይኑ እየቃኘ ሲያዳምጥ፣ "መሸብህ ሂድ! በጐችህም እንዳይጠፉብህ" አሉትና በአንድ እጃቸው ራሱን ዳበሱት። ዓሊ በከራር ፍቅር ያኔ ነበር የተለከፈው።

መመሪያ አንድ ፦ <u>ከጥያቄ **1-1**0 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።</u>

1. የመጀመሪያው አንቀፅ የቀረበበት የአግባፍ ስልት ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
   ሀ. የትረካ ስልት ለ. የብያኔ ስልት ሐ. የገለፃ ስልት መ. የንፅፅር ስልት
2. ዓሊ ወደሽማግሌው ቤት በፍጥነት መሄድ ያልቻለው በምን ምክንያት ነው?
   ሀ. ፍርሃትና ድንጋጤ ዓሊን ወሮት ስለነበረ
   ለ. ዓሊ ሽማግሌው ያባርሩኛል ብሎ ሰግቶ ስለነበር
   ሐ. ከከራሩ የሚወጣው ድምፅ ዓሊን ማርኮት ስለነበር
   መ. ወደ ሽማግሌው ቤት የሚወስደው መንገድ አስቸጋሪ ስለነበረ
3. በምንባቡ ሁለተኛው አንቀፅ አራተኛው ዐ.ነገር ውስጥ ".... ቃኘው" የሚል ቃል ተጠቅሷል። በአገባቡ መሠረት ትርጉሙ ምንድን ነው?
   ሀ. አተኮረው፣አየው ሐ. አቃናው፣ አስማማው
   ለ. ሰለለው፣ገረመመው መ. መዘነው፣ ገመተው
4. በምንባቡ አራተኛው አንቀፅ ውስጥ "የጳጳስ ቆብ" እና "ዳዲሞስ ተራራ" _____። ክፍት ቦታውን ሊያሟላ የሚችል ትክክለኛ አማራጭ ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?
   ሀ. ጎልተዋል ለ. ተነፃፅረዋል ሐ. ተመሰለዋል መ. ተቃርነዋል
5. በሁለተኛው አንቀፅ ውስጥ ዓሊ በከራር የመጫወት ችሎታ ያለው መሆኑ ተገልጿል። ዓሊ የከራር ፍቅር እንዲያድርበት ያደረገው ማን እንደሆነ የሚያመለክተው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው?
   ሀ. አባቱ ለ. እናቱ ሐ. አቦ ዳዲሞስ መ. አቦ ፋርጤ
6. በምንባቡ ሦስተኛ አንቀፅ ውስጥ "..... በሐሩር ጉልበት ተሸንፎ....." የሚለው ሐረግ ትርጉም ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
   ሀ. የስራ ጫና አስጐንብሶት ሐ. ጉልበተኛ ደብድቦ ጥሎት
   ለ. የፀሐይ ግለት አድክሞት መ. በሐሩር ክንድ ስር ወድቆ

7. የባለታሪኩ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለፀው ባለታሪኩ በምን ሁኔታ ውስጥ እያለ እንደነበር የሚያመለክተው አማራጭ ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?

ሀ. በልቡ የሚያዳምጠውን ዜማ ለመውለድ አካባቢውን ሲማትር

ለ. ከሽማግሌው እግር ስር ተቀምጦ ክራር ሲያዳምጥ

ሐ. ሽማግሌው "መሸብህ ሂድ!" ብለው ራሱን ሲዳስሱ

መ. እናቱ ሞተውበት እንደጓደኞቹ በጎች ሲጠብቅ

8. በአምስተኛው አንቀፅ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው የሚታዩት የሥርዓተ ነጥብ አይነቶች ስንት ናቸው?

ሀ. ሁለት ለ. ሦስት ሐ. አራት መ. አምስት

9. በምንባቡ ውስጥ ፀሐፊው " እረኝነትን" የገለፀበት ድባብ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

ሀ. እረኝነት በገጠር፣ በግብርና መስክ ታዋቂነት ያተረፈ ስራ እንደሆነ ተጠቷል

ለ. እረኝነት በገጠር፣ የልጆች የዘለቄታ ህይወት እንቅፋት እንደሆነ ተጠቷል

ሐ. እረኝነት በገጠር፣ የልጆች የግብርና ሙያ መለማመጃ መስመር እንደሆነ ተጠቷል

መ. እረኝነት በገጠር፣ የልጆች የብሩህ ተስፋ ምልክት እንደሆነ ተጠቷል

10. ባለታሪኩ በክራር ፍቅር ስለመለከፉ የሚገልፀውን ሐሣብ የያዘው ስንተኛው አንቀፅ ነው?

ሀ. ሁለተኛው አንቀፅ ለ. ሦስተኛው አንቀፅ ሐ. አራተኛው አንቀፅ መ. አምስተኛው አንቀፅ

መመሪያ ሁለት ፦ <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ምረጥ(ጭ)።</u>

11. ከሚከተሉት መካከል ኃላፊ ጊዜን የሚያመለክት ግስ የትኛው ነው?

ሀ. ሰብሮ ነበር ለ. ሰብሯል ሐ. እየሰበረ ነው መ. ሀና ለ መልስ ናቸው

12. ‹‹አገኝ›› የሚለው ቃል በሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ዖታ ሲፃፍ የቱ ነው?

ሀ. አገኘች ለ. አገኙ ሐ› አግኝቷል መ. አገኘህ

13. የጋራ መጠሪያ (ጅምላዊ) መጠሪያ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የተፅኦ ስም ለ. የወል ስም ሐ. የረቂቅ ስም መ. ነገር ስም

14. ከሚከተሉት ውስጥ ጥገኛ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በሬ ለ. ኣችን ሐ. ቤት መ. ሰው

15. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ቅፅል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቀይ ለ. ልዑል ሐ. ጥቁር መ. ሰማያዊ

16. አንድ ኃይለቃል ከአንቀፅ መጨረሻ ሲመጣ የሚይዘው ቅርፅ የቱ ነው?

ሀ. ለ. ሐ. መ.

17. ሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. እሷ ለ. እኛ ሐ. እኔ መ. አንቺ

18. የስነ ቃል ባህሪ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ክዋኔ ለ. ተለዋዋጭነት ሐ. በቃል መተላለፍ መ. ሁሉም

19. ነፃ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰው ለ. ቤቶች ሐ. በጎች መ. ሰዎች

20. የአንቀፅ ባህሪ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አንድነት ለ. ውህደት ሐ. አፅንኦት መ.. ሁሉም

21. ‹‹ዱባ›› ለሚለው ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. ተቀቅሎ የሚበላ ለ. ወፍራም ሐ. ቀጭን መ. ሁሉም

22. የአረፍተ ነገር መግቻ መሆን፣ የባለቤት አመልካች ቅጥያ ምዕላድን በውስጡ ማቀፍ ከሌሎች የቃል ክፍሎች ልዩ ይሆናል የሚባለው _____ ነው።

ሀ. ስም ለ. ግስ ሐ. ቅፅል መ. ተውሳከ ግስ

23. ከግስ በፊት ቀድሞ እየገባ የቃል ክፍሉን ከጊዜ ፣ ከሁኔታ ፣ ከቦታ ይገልፃል።

ሀ. ስምና ቅፅል ለ. ተውሳከ ግስ ሐ. መስተዋድድ መ. ቅፅል

24. በአረፍተነገር ውስጥ አይቀሬ ተደርገው የሚወሰዱ የቃል ክፍሎች_____እና ___ናቸው።

ሀ. ስምና ቅፅል ለ. ግስና ቅፅል ሐ. ስምና ግስ መ. የተውሳከ ግስና መስተዋድድ

25. ጠንክሮ የሰራ ሰው ከድህነት እንደሚላቀቅ <u>እሙን</u> ነው። የተሰመረበት ቃል የምን ገላጭ ነው

ሀ. የስም ለ. የግስ ሐ. የቅፅል መ. ተውሳከ ግስ

26. የድርሰት ዋና አካል _____ ነው።

ሀ. ሀተታ ለ. መግቢያ ሐ. መደምደሚያ መ. ሁሉም

27. የቋንቋ አነስተኛ ክፍል ወይም ቅንጣት _____ ይባላል።

ሀ. ቃል ለ. አረፍተነገር ሐ. ምዕላድ መ. ሀረግ

28.ከስነ ቃል የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. አፈታረክ ለ. እንቆቅልሽ ሐ. ግጥም መ. ተረት

29.አንቀፅ ለመግፍ በቅድሚያ _____ ማዘጋጀት አለብን።

ሀ. ሀይለ ቃል ለ. ወረቀት ሐ. አስተዋፅኦ መ. መዘርዝር

30.የአንቀፁን ሀሳብ አጠቃሎ የሚይዝ አረፍተ ነገር _____ ይባላል።

ሀ. መዘርዘር አረፍተነገር ሐ. ዋና አረፍተ ነገር

ለ. ተራ አረፍተነገር መ. ውስብስብ አረፍተ ነገር

31.ጥገኛ ምዕላድ ከሚገኙበት ቦታ አንፃር በ _____ ይከፈላል።

ሀ. አራት ለ. ሁለት ሐ. አምስት መ. ሶስት

32._____ ማለት አንድ ዋና ሀሳብ የሚተላለፍበት የአረፍተ ነገሮች ድምር ውጤት ነው።

ሀ. ድርሰት ለ. ሀይለ ቃል ሐ. አንቀፅ መ. መግቢያ

33.ከሚከተሉት ውስጥ ባለንብረትነትን የሚያመለክተው ምዕላድ የቱ ነው?

ሀ. ኦች ለ. ኣችን ሐ. ኣት መ. ዎች

34." እሳት ገባው "ለሚለው ፊሊጣዊ ንግግር ፍቺ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ተበሳጨ ለ. በሰለ ሐ. በሸቀ መ. ተጨነቀ

35." በለስ ቀናው " ለሚለው ፊሊጣዊ ንግግር ፍች የቱ ነው ?

ሀ. ተሳካለት ለ. ወፈረ ሐ. ዳነ መ. ሀገሩ ገባ

መመሪያ አራት ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ የሚሆነውን መልስ ምረጥ(ጭ)።

36.ሸነገለ

ሀ. አቆላመጠ ለ. አመሰገነ ሐ. ተለማመጠ መ. አሞኘ

37.ፍርጃ

ሀ. ዳኝነት ለ. እርግማን ሐ. እድል መ. መከራ

38.ደራ

ሀ. ሰፋ ለ. ዳበረ ሐ. ሞቀ መ. ተስማማ

39.እንከን

ሀ. ስጦታ ለ. ሰሃ ሐ. ጥርጣሬ መ. ንፁህ

40.ልጨኛ

ሀ. ደስተኛ ለ. አስማተኛ ሐ. ቁምነገረኛ መ. የተላጠ